በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት
ፍትህ ቢሮ
የህግ ምክር፣ማርቀቅና ማጠቃለል ዳይሬክቶሬት

THE AMAHARA NATIONAL REGIONAL STATE
JUSTICE BUREAU
LEGAL COUNSELING, DRAFTING AND COMPILATION
DIRECTORATE

ቁጥር
Ref. No የህ/ም/ማጠ/ዳ/1478/18
ቀን
Date 25/12/2018 ዓ.ም

ለአማራ ክልል ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ

ባህር ዳር፤

ጉዳዩ፦ መመሪያ ምዝገባን ይመለከታል

በአማራ ክልል የአስተዳደር ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 313/2018 ዓ.ም ላይ እንደተደነገገው ማንኛውም የአስተዳደር ተቋም አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በሥራ ላይ የነበሩ መመሪያዎችን አዋጁ በወጣ በ2 (ሁለት) ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለፍትህ ቢሮው በመላክ እንዲመዘገብ ማድረግ እንዳለበት ተደንግጓል።

በዚህ መሰረት ቢሮው በቁጥር ን/ዘ/ም/100/867/18 በቀን 18/12/2018 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ የንግድ ትርኢትና ባዛር ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 04/2011 ዓ.ም ምዝገባ እንዲከናወን መላኩ ይታወሳል።

ስለሆነም ፍትህ ቢሮ በአዋጅ ቁጥር 292/2017 ዓ.ም አንቀጽ 16 ንዑስ አንቀፅ 1 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የተላከለትን መመሪያ ቁጥር 04/2011 ዓ.ም ሕጋዊነቱን፣ መሰረታዊ መብቶችና መርሆችን የማይጥስ መሆኑን መርምሮና አስተካክሎ መመሪያው በክልል ደረጃ መመሪያ ቁጥር 168/2018 ዓ.ም ሆኖ ስራ ላይ እንዲወል የመዘገበው ስለሆነ የተመዘገበውን መመሪያ ቅጂ 14 ገጽ በዚህ ሸኚ ደብዳቤ አባሪ በማድረግ የላክን መሆኑን እንገልጻለን።

ከሰላምታ ጋር

የህግ ም/ማ/ማ/ ዳይሬክቶሬት
ዳይሬክተር

ግልባጭ//

- ለቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት፤ (ያለ አባሪ)
- ለፍት/ሕግ ጉዳ/ዘር/ምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽሕፈት ቤት

ፍትሕ ቢሮ

Tel.No 058 222 0794/793
☎ 058 220 37 57
✉ 995
Fax- 0582221530

መመሪያ ቁጥር 168/2018 ዓ.ም

የአማራ ክልል የንግድ ትርኢት እና ባዛር አፈጻጸም መመሪያ

በሀገራችን ኢትዮጵያ የነፃ ገበያ የኢኮኖሚ ፖሊሲ መሠረት ለማንኛውም የንግድ ሥራ መስክ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር አስፈላጊ ስለሆነ የንግድ ምዝገባና የንግድ ሥራ ፈቃድ አሰጣጥ ስርዓት የነፃ ገበያ ኢኮኖሚውን ተከትሎ የንግዱ ሕብረተሰብ ከመንግሥት ሊያገኝ የሚገባውን አገልግሎት ለማቀላጠፍና የአገልግሎት አሰጣጡ ኢኮኖሚያዊ እድገትን እንዲያስገኝ የአሰራር ማሻሻያ ማድረግ በማስፈለጉ፤

የአማራ ክልልን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበና የሁሉንም ወገን ተጠቃሚነት ባረጋገጠ መልኩ ምርትና አገልግሎትን ለማሳደግ፣ የፈጠራ ሥራዎችን ለማስተዋወቅ፣ የኢንቨስትመንት ዕድሎችን ለመፍጠር እንዲሁም የክልሉን የኢንዱስትሪና የግብርና ምርታማነትን ለማሻሻል፣ ቴክኖሎጅን ለማሸጋገር፤ የሀሣብ ልውውጦችን ለማዳበር፣ በምርትና አገልግሎት ላይ ያተኮረ የሻጭና የገዥ የአገልግሎት አድማስን ለማስፋፋት እና የህጋዊ ንግድን ለማስፋፋት ሥርዓቱ የሚመራበት ሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት በማስፈለጉ

ስራ ላይ በነበረዉ መመሪያ ላይ የታዩ የአሰራር ክፍተቶች ማለትም በአዘጋጁ፣ በፕሮሞተሩና በፈቃድ ሰጪዉ አካል መካከል ያሉ መብቶችና ግዴታዎችን በተሟላ መልኩ በመዘርዘር ግቡን ሊያሳካ የሚችል የንግድ ትርኢትና ባዛር ዝግጅት እንዲኖር ለማስቻል ያመች ዘንድ መመሪያዉን ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የአማራ ክልል ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ገበያ ልማት ቢሮ በአዋጅ ቁጥር 230/2008 አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 1 (ሠ) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአማራ ክልል የንግድ ትርኢትና ባዛር ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 168/2018 ተብሎ" ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፦

1/ "ቢሮ" ማለት የአብክመ ንግድ፣ ኢንዱስትሪና ገበያ ልማት ቢሮ ማለት ነው፤

2/ "የንግድ ትርዒት" ማለት በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ መሠረት በክልሉ ውስጥ የሚዘጋጅ የአገር ዉስጥ ምርትን ወይም የውጭ አገር ምርትን ወይም ሁለቱንም በያዘ መልኩ ንግድን የማስፋፋት ዓላማ ያለውና፣ ለተወሰኑ ቀናት ብቻ የንግድ ዕቃዎችን፣ መሣሪያዎችን፣ የኢንዱስትሪና የግብርና ውጤቶችንና ልዩ ልዩ አገልግሎቶችን ወዘተ ለህዝብ እይታ ወይም ለሽያጭ በማቅረብ የሚካሄድ ተግባር ነው፤

3/ "ባዛር" ማለት ከመደበኛ የመሸጫ ቦታ ውጭ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት በተከለለ መልኩ በተወሰነ ጊዜ ዕቃዎችንና አገልግሎቶችን በማሳየትና በማስተዋወቅ ሽያጭ ወይም የንግድ ልዉዉጥ የሚካሄድበት ቦታ ወይም ድርጊት ነው፤

4/ "ተጓዥ የሆነ የንግድ ትርኢትና ባዛር ማለት" ባዛር አዘጋጁ ከአንድ ከተማ/ወረዳ ወደ ሌላ ከተማ/ወረዳ እየተዘዋወረ የሚያካሂደው ባዛር ማለት ነው፤

5/ "ተጓዥ ያልሆነ የንግድ ትርኢትና ባዛር ማለት" ባዛር አዘጋጁ አንድ ከተማ/ወረዳ/ ላይ ብቻ የሚያካሂደው ባዛር ማለት ነው፤

6/ "የንግድ ኤግዚቢሽን ማለት" ማለት ለአንድ የተወሰነ ዓላማ ለተወሰነ ጊዜ የሚቆይ የተመረጡ ምርቶችና አገልግሎቶችን ለህዝብ እይታ ማቅረብና ማስተዋወቅ ማለት ነው፤

7/ "ነጋዴ" ማለት የሙያ ሥራው አድርጎና ጥቅም ለማግኘት ሲባል በንግድ ሕጉ አንቀጽ 5 የተዘረዘሩትን ሥራዎች የሚሠራ ወይም አገልግሎት የሚሰጥ ወይም የንግድ ሥራ ነው ተብሎ በሕግ የሚወሰነውን ሥራ የሚሠራ ማንኛውም ሰው ነው

8/ "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

9/ "አዘጋጅ" ማለት ተጓዥ የሆነ ወይም ተጓዥ ያልሆነ የንግድ ትርኢትና ባዛር እንዲሁም ኤግዚቢሽን ለማዘጋጀት ማመልከቻ ያቀረበ የመንግስት ተቋማት፣ ህዝባዊ ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ይህም መንግስታዊ ተቋማት፣ ንግድና ዘርፍ ማህበራት፣ የዘርፍ ማህበራት፣ የነጋዴ ሴቶች ማህበራት፣ ህብረት ስራ ማህበራትና ሌሎች ከንግድ ጋር ግንኙነት ያላቸዉ ልዩ ልዩ ህዝባዊ ማህበራትን ያካትታል፤

10/ "ማመልከቻ" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት ተጓዥ የሆነ ወይም ተጓዥ ያልሆነ የንግድ ትርኢትና ባዛር እና ኤግዚቢሽን ለማዘጋጀት ፈቃድ እንዲሰጠዉ የፈለገ አካል ለቢሮዉ የሚያቀርበዉ የዝግጅቱን ዝርዝር አላማ የያዘ የጽሁፍ ጥያቄ ነው፤

11/ "ፈቃድ" ማለት በዚህ መመሪያ መሠረት ተጓዥ የሆነ ወይም ተጓዥ ያልሆነ የንግድ ትርኢትና ባዛር ለማካሄድ እንዲቻል በቢሮው አማካኝነት ለአዘጋጁ የሚሰጥ የጽሐፍ ማረጋገጫ ነው፤

12/ "ልዩ ፈቃድ ማለት" ለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት፣ ለአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራዞች፣ ለህብረት ስራ ማህበራትና ዩኒየኖች ተጓዥ የሆነ ወይም ተጓዥ ያልሆነ የንግድ ትርኢትና ባዛር ለማካሄድ እንዲቻል በቢሮው አማካኝነት ለአዘጋጁ የሚሰጥ የጽሐፍ ማረጋገጫ ነው፤

13/ "ውል" ማለት ተጓዥ የሆነ ወይም ተጓዥ ያልሆነ የንግድ ትርዒትና ባዛር ለማካሄድ ፈቃድ የተሰጠው አዘጋጅ ስለ ንግድ ትርዒትና ባዛሩ አጠቃቀም ሁኔታ የተዘረዘሩ መብቶችና ግዴታዎችን ለማክበር በፈቃድ ሰጪዉ ቢሮና በፈቃድ ተቀባዩ አካል መካከል እንዲሁም በአዘጋጁና በጥሮሞተሩ መካከል የተፈረመ የስምምነት ሰነድ ነው፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በሁሉም አካባቢዎች ተጓዥ የሆነ ወይም ተጓዥ ያልሆነ የንግድ ትርዒትና ባዛር እንዲሁም ኤግዚቢሽን በሚያዘጋጁ አካላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

የንግድ ትርኢትና ባዛር ፈቃድ አሰጣጥ መስፈርቶች

4. ተጓዥ የሆነ ወይም ተጓዥ ያልሆነ የንግድ ትርኢትና ባዛር ፈቃድ ሲሰጥ ሊሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶች

1/ አዘጋጁ ስለንግድ ትርኢቱና ባዛሩ ዓላማና ዝርዝር አፈጻጸም የሚገልጽ እቅድ፣ ፕሮፖዛል እንዲሁም ፈቃድ እንዲሰጠዉ ማመልከቻ አያይዞ ማቅረብ አለበት፤

2/ ፈቃድ ጠያቂው ህጋዊ ስለመሆኑ የሚያስረዳና ከሚመለከተዉ መንግስታዊ አካል የተሰጠዉ ሰርተፍኬት ሊኖረዉና ሊያቀርብ ይገባል፡፡ ህዝባዊ የሆኑ ድርጅቶችና የሙያ ማህበራት ህጋዊ ሰዉነት ያገኙበትን ሰርተፍኬት አያይዘዉ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሆኖም ምርትና አገልግሎትን ለማስተዋወቅና ዘላቂ የገበያ ትስስር እንዲኖር ለማድረግ የንግድ ትርኢትና ባዛር የሚያዘጋጁ መንግሥታዊ ተቋማት የህጋዊነት ሰርተፍኬት አይመለከታቸውም፤

3/ የንግድ ትርኢትና ባዛርን የሚያዘጋጀዉ አካል ጥያቄዉን በሚያቀርብበት ጊዜ ከሚዘጋጅበት ከተማ/ወረዳ የከንቲባ ወይም አስተዳዳሪ ከጊዜያዊ የማሳያ ቦታ መኖር፣ ከጸጥታና ጥበቃ ጋር በተያያዘ የስምምነት ወይም የድጋፍ ደብዳቤ አያይዘዉ ማቅረብ አለባቸው፤

4/ አዘጋጁ ፕሮሞተር የሚቀጥር ከሆነ ፕሮሞተሩ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ያለዉ ስለመሆኑ ማረጋገጫ ማቅረብ ያለበት ሲሆን ፕሮሞተሩ የሚመረጠው ቢያንስ ሶስት ተወዳዳሪዎችን በመጋበዝ በድርድር ነው፡፡ ይሄም ሆኖ የፕሮሞተሩ የኮሚሽን ክፍያ ቢበዛ ከተጣራ ትርፉ 25 ከመቶ በላይ መሆን አይችልም፤

5/ አዘጋጁ ከፕሮሞተሩ ጋር ያደረገዉን ዝርዝር የዉል ስምምነት አብሮ ማቅረብ ይጠበቅበታል፤

6/ የአዘጋጁና የፕሮሞተሩ ውል ባዛሩ በሚካሄድበት ወረዳ ወይም ከተማ አስተዳዳር ንግድ ጽ/ቤት ሃላፊ በእያንዳንዱ ገጽ ላይ ፊርማና ክብ ማህተም ተቀምጦበት መጽደቅ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ግን አዘጋጁ የክልሉ ዘርፍ ማህበር፣ ዘርፍ ማህበር ም/ቤት፣ የክልሉ ን/ዘ/ማ/ም/ቤት፣ የክልሉ ነጋዴ ሴቶች ማህበር፣ የክልል መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በሚሆንበት ጊዜ ውሉ የሚጸድቀው በክልሉ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ይሆናል፤

7/ የክልሉን እድገት ሊያፋጥኑና ሊያበረታቱ የሚችሉ የንግድ ትርኢትና ባዛር ለሚያዘጋጁ አካላት ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ይህም በንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ከፍተኛ አመራሮችና ባለሙያዎች በጋራ ይወሰናል፤

8/ ከላይ በዝርዝር የቀረቡት መስፈርቶች እንደተጠበቁ ሆኖ የአዘጋጆች የማመልከቻ አቀራረብ ቅድሚያ ግምት ውስጥ ይገባል፡፡ ይህም የሚሆነዉ ማሟላት ያለበትን ሰነዶች አሟልቶ እንዲያቀርብ የተጠየቀ አዘጋጅ ከተነገረው እለት ጀምሮ ከ 7 ቀናት በላይ የሚዘገይ ከሆነ የተያዘለት ወረፋ ዉድቅ ሆኖ ለቀጣዩ ባለወረፋ እድሉ ይሰጣል፤

9/ የንግድ ትርኢትና ባዛር አዘጋጆች በተናጠል ወይም በጋራ ተግባሩን ሊያከናዉኑ ይችላሉ፡፡ ሆኖም በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ በአንድ ከተማ ላይ የንግድ ትርኢትና ባዛር የሚካሄደው ለ 3 ጊዜ ብቻ ይሆናል፡፡ ነገር ግን አሳማኝና አስገዳጅ ሁኔታ ከኖረ የንግድ ቢሮ ሃላፊዎች ሲፈቅዱ ብቻ የሚፈጸም ይሆናል፤

10/ ፈቃድ ጠያቂዉ ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት፣ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና የነጋዴ ሴቶች ማህበር ከሆኑ የንግድ ትርኢትና ባዛር ከሚካሄድበት ከተማ/ወረዳ የከንቲባ ወይም የአስተዳዳሪ የድጋፍ ደብዳቤ አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡ ባዛሩን የጠየቀው ከላይ ከተጠቀሱት ውጭ ከሆነ ደግሞ ባዛሩ ከሚካሄድበት ከተማ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት፣ ከዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና ከከንቲባ ወይም ከአስተዳዳሪ የድጋፍ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ የዘርፍ ማህበራት ም/ቤት እና የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ሌሎች የባዛር አዘጋጆች የድጋፍ ደብዳቤ ሲጠይቁ በተጠየቁ ቀናቶች ውስጥ ሁለት ምክር ቤቶች ራሳቸው አዘጋጅ እስካልሆኑ ድረስ የድጋፍ ደብዳቤ የመስጠት ግዴታ አለባቸው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ምክር ቤቶች የድጋፍ ደብዳቤ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ኃላፊዎች የከንቲባውን ወይም የአስተዳዳሪውን የድጋፍ ደብዳቤ መሰጠቱን ካረጋገጠ በኋላ የባዛር ፈቃዱ እንዲሰጥ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፤

11/ ተጓዥ የሆነ የንግድ ትርኢትና ባዛር የሚያዘጋጅ አካል ባዛሩን ተንቀሳቅሶ በሚያካሂድባቸው ከእያንዳንዱ ከተማ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት፣ ከዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት እና ከከንቲባ ወይም ከአስተዳዳሪ የድጋፍ ደብዳቤ በአንድ ላይ አጠቃሎ ከጥያቄው ጋር ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

5. ልዩ የባዛር ፈቃድ ሲሰጥ ሊሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶች

1/ ፈቃድ ጠያቂው ህጋዊ ስለመሆኑ የሚያስረዳና ከሚመለከተዉ መንግስታዊ አካል የተሰጠዉ ሰርተፍኬት ሊኖረዉና ሊያቀርብ ይገባል፡፡ ህዝባዊ የሆኑ ድርጅቶችና የሙያ ማህበራት ህጋዊ ሰዉነት ያገኙበትን ሰርተፍኬት አያይዘዉ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሆኖም ምርትና አገልግሎትን ለማስተዋወቅና ዘላቂ የገበያ ትስስር እንዲኖር ለማድረግ የንግድ ትርኢትና ባዛር የሚያዘጋጁ መንግሥታዊ ተቋማት የህጋዊነት ሰርተፍኬት አይመለከታቸውም፤

2/ የንግድ ትርኢትና ባዛርን የሚያዘጋጀዉ አካል ጥያቄዉን በሚያቀርብበት ጊዜ ከሚዘጋጅበት ከተማ/ወረዳ አስተዳደር ወይም ከንቲባ ጽ/ቤት ከጊዜያዊ የማሳያ ቦታ መኖር፣ ከጸጥታና ጥበቃ ጋር በተያያዘ የስምምነት ወይም የድጋፍ ደብዳቤ አያይዘዉ ማቅረብ አለባቸዉ፤

3/ አዘጋጁ ፕሮሞተር የሚቀጥር ከሆነ ጋር የዉል ስምምነት አብሮ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

6. የንግድ ኤግዚቢሽን ፈቃድ ሲሰጥ ሊሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶች

1/ ፈቃድ ጠያቂው ህጋዊ ስለመሆኑ የሚያስረዳና ከሚመለከተዉ መንግስታዊ አካል የተሰጠዉ ሰርተፍኬት ሊኖረዉና ሊያቀርብ ይገባል፡፡ ህዝባዊ የሆኑ ድርጅቶችና የሙያ ማህበራት ህጋዊ ሰዉነት ያገኙበትን ሰርተፍኬት አያይዘዉ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ሆኖም ምርትና አገልግሎትን ለማስተዋወቅ እንዲኖር ለማድረግ የሚያዘጋጁ መንግሥታዊ ተቋማት የህጋዊነት ሰርተፍኬት አይመለከታቸውም፤

2/ የንግድ ኤግዚቢሽን የሚያዘጋጀዉ አካል ጥያቄዉን በሚያቀርብበት ጊዜ ከሚዘጋጅበት ከተማ/ወረዳ በከንቲባ ወይም በአስተዳዳሪ የስምምነት (የድጋፍ) ደብዳቤ አያይዘዉ ማቅረብ አለባቸዉ፤

3/ አዘጋጁ ፕሮሞተር የሚቀጥር ከሆነ ጋር የዉል ስምምነት አብሮ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

7. <u>የአዘጋጁና የተሳታፊ ነጋዴዎች ግዴታዎች</u>

1/ አዘጋጁ የንግድ ትርኢትና ባዛር ከማካሄዱ በፊት በቅድሚያ ከንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ፈቃድ ማዉጣት ይጠበቅበታል።ለዚህም በንግድ ምዝገባና ፈቃድ በኩል የአገልግሎት ታሪፍ ክፍያ በደንብ ቁጥር 102/2004 የተቀመጠውን የአገልግሎት ክፍያ ለክልሉ ንግድ ቢሮ መክፈል ይጠበቅበታል፤

2/ ማንኛውም ባዛር አዘጋጅ አካል የባዛር ፈቃዱን ባዛሩ ከሚዘጋጅበት ከ 10 ቀን በፊት ከፈቃድ ሰጭው አካል መውሰድ ይጠበቅበታል፤

3/ በንግድ ትርኢትና ባዛር እንዲሣተፉ የሚጋበዙ ነጋዴዎች፣ድርጅቶች ፣ካምፓኒዎች ወዘተ የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸውና በበጀት አመቱ የታደሰ ፈቃድ ያላቸው ብቻ ይሆናሉ። ያለ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ባዛር ላይ መሳተፍ ክልክል ነው፤

4/ በባዛሩ ግብይት የሚፈጽሙ አካላት በንግድ ድርጅታቸው ስም የታተመ ህጋዊ ደረሰኝ ለደንበኞች የመስጠት ግዴታ አለባቸው።ያለ ህጋዊ ደረሰኝ ባዛር ላይ መሳተፍ ክልክል ነው። በደረሰኝ ግብይት የመፈጸም ግዴታ ያለባቸው ደረጃ ሀ እና ደረጃ ለ ድርጅቶች ብቻ ናቸው፤

5/ ተጓዥ የሆነ ወይም ተጓዥ ያልሆነ የንግድ ትርኢትና ባዛር ለማዘጋጀት የሚቀርብ ጥያቄ ባዛሩ ይከናወናል ተብሎ ከታቀደበት ከ 3 ወር በፊት ለንግድ ቢሮ መቅረብ ይኖርበታል። ከ 3 ወር በፊት ያልቀረበ የባዛር ጥያቄ አይስተናገድም፤

6/ ተጓዥ የሆነ የንግድ ትርኢትና ባዛር የሚካሄድባቸው ከተሞች ምንም እንኳ ከተማው ላይ ያለ አካል ራሱ አዘጋጅ ባይሆንም ባዛሩ በዚያው ከተማ ላይ እስከተካሄደ ድረስ ከተማው የባዛር እድል እንደተሰጠው ተቆጥሮ በድግግሞሹ የሚመዘገብ ይሆናል፤

7/ ተጓዥ የሆነ ወይም ተጓዥ ያልሆነ የንግድ ትርኢትና በዛር ፈቃድ የቆይታ ጊዜ በአንድ ከተማ/ወረዳ/ ላይ ከ 10 ተከታታይ ቀናት መብለጥ የለበትም። ሆኖም በአዘጋጅ አካል ጥያቄው ሲቀርብና መራዘሙ አስፈሊጊ ሆኖ ሲገኝ ፈቃዱን የሰጠዉ አካል ካመነበት እንዲስፈሊጊነቱ እስከ 3 ቀናት ሊራዘም ይችላል። የተፈቀደውን ተጨማሪ 3 ቀናት አልፎ በራሱ ጊዜ የንግድ ትርኢትና ባዛሩን ያስቀጠለ አዘጋጅ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፤

8/ ተጨማሪ 3 ቀን የተፈቀደለት ባዛር አዘጋጅ የአገልግሎት ክፍያ ለክልሉ ንግድ ቢሮ ብር 300 /ሶስት መቶ ብር/ መክፈል ይጠበቅበታል፤

9/ በአንድ ቀጠና ውስጥ በተመሳሳይ ጊዜ ሁለት የባዛር ፈቃድ አይሰጥም። ቀጠናውም ምዕራብ አማራና ምስራቅ አማራ ተብሎ የተከፋፈለ ነው። ሆኖም ግን በአንድ ቀጠና ውስጥ ተመሳሳይ የባዛር ጥያቄ ሲቀርብ የቢሮ ኃላፊው የቦታውን ርቀትና የባዛሩን ጠቀሜታ ግምት ውስጥ በማስገባት ሊፈቅድ ይችላል። በአንድ ቀጠና ውስጥ በተከታታይ የሚካሄዱ ባዛሮች ፈቃድ ሲሰጥ የመጀመሪያው እንዳለቀ ሁለተኛው አዘጋጅ ከ6 ቀናት በፊት ባዛሩን ማካሄድ አይቻልም፤

10/ ማንኛውም በክልሉ ውስጥ በሚካሄደው የንግድ ትርኢትና ባዛር ላይ የሚሳተፍ ፕሮሞተር ሊኖረው የሚገባ የንግድ ስራ ፈቃድ፡- የልዩ ዝግጅት ማስተባበር ፈቃድ መስጫ መደብ/74150/፣ የማስታወቂያ ስራ ፈቃድ መስጫ መደብ/89500/ እና የንግድ ፕሮሞሽን አገልግሎት ፈቃድ መስጫ መደብ/74160/ ሶስቱም የንግድ ስራ ፈቃድ ያለው ሆኖ ፈቃዶቹ በበጀት ዓመቱ የታደሱና የፀኑ የንግድ ስራ ፈቃዶች መሆን ይገባቸዋል፤

11/ አዘጋጁ አካል የንግድ ትርኢትና ባዛር በሚካሄድበት ከተማ ላይ ከጠቅላላ ተሳታፊ ነጋዴዎች መካካል ቢያንስ 10% የሚሆኑ ነጋዴዎች እንዲሳተፉ የማድረግና የማሳያ ቦታ ኪራይ ክፍያም ከሌላ አካባቢዎች ከመጡ ነጋዴዎች ክፍያ ቢያንስ 10% ቅናሽ በማድረግ ማበረታታት ይገባዋል፤

12/ አዘጋጁ አካል የንግድ ትርኢትና ባዛር ዝግጅቱን አዘጋጅቶ ከፈፀመ በኋላ በታቀደው መሰረት ባዛሩ ስለመካሄዱ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ዝርዝር የአፈጻጸም ሪፖርት ማቅረብ አለበት። እንዲሁም የባዛሩን አፈጻጸም የኦዲት ሪፖርት በ2 ወር ዉስጥ የማቅረብ ግዳታ አለበት። በተባለዉ አግባብ ሪፖርት የማያቀርብ አዘጋጅ አስፈላጊው አስተዳደራዊ ርምጃ ይወሰድበታል፤

13/ አዘጋጁ በተፈቀደለት ጊዜ ባዛሩን ማካሄድ ካልቻለ ወይም በተሰጠው ፈቃድ መጠቀም አለመቻሉን ካረጋገጠ ከበቂ ምክንያትና ማስረጃ ጋር ትርኢቱ ይከፈታል ተብሎ ከታሰበበት ጊዜ አንድ ወር አስቀድሞ ለቢሮው የማሣወቅ ግዴታ አለበት። ሆኖም ባዛሩ ስለመቋረጡ ወይም መቅረቱ እንዲሁም ስለመራዘሙ ቅስቀሳ ባደረገበት የማስታወቂያ ዘዴ ለህዝቡ ማሣወቅ ይኖርበታል የባዛር ዝግጅቱ ሳይካሄድ የሚቀር ከሆነ ከተለያዩ አካላት በስፖንሰርነት የተሰበሰበ (የተገኘ) ገቢ መመለስ አለበት። አዘጋጁ እነዚህን ተግባራት ካልፈጸመ አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ ይወሰድበታል፤

14/ አዘጋጁ የንግድ ትርኢት የሚዘጋጅበትን ቦታ ለተገልጋዩ አመች የሆነና ከጸሃይ፣ ከአቧሯና ከነፋስ የሚከላከል መጠለያ እንዲኖረው፣ በሰው በጤናና ደህንነት ላይ ችግር የማያስከትል እንዲሆን፣ በባዛሩ ቆይታ ጊዜ በአምራቾች፣በነጋዴዎችና በሸማቾች መካካል የሚካሄደውን የንግድ ልውውጥ የማያቋርጥ እንዲሁም የአካባቢ ኗሪዎችን ጸጥታና ደህንነት የማያውክ እንዲሆን ማመቻቸት አለበት፤

15/ የንግድ ትርኢትና ባዛር የማዘጋጀት ጥያቄ በማቅረብ የተፈቀደለት ድርጅት ወይም አካል ፈቃዱን ካገኘበት ቀን ጀምሮ ከንግዱ ማህበረሰብ ለመመዝገቢያ፣ ለቦታ ኪራይ፣ ለቲኬት ሽያጭና ለመሳሰሉት የገቢ ማሰባሰቢያ ርዕሶች ያሰባሰበዉን ገንዘብ ለታለመለት ዓላማ የማዋል ግዴታ ያለበት ሲሆን ገቢ ከሰበሰበ በኋላ ዝግጅቱን (ባዛሩን)ገንዘቡን ለታለመለት ዓላማ ባያውል በዚህ ዝግጅት ዉስጥ ተዋናይ የሆኑ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች በህግ አግባብ ተጠያቂ እንዲሆኑ ይደረጋል፤

16/ አዘጋጁ በባዛሩ ቆይታ ወቅት በህብረተሰቡና በንብረት ላይ ማንኛውም አደጋ (ቃጠሎ፣ የኤሌክትሪክ ሾክ፣ ዝርፊያ፣ ድብደባ ወዘተ) እንዳይደርስ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የመስራት ግዴታ አለበት፤

17/ አዘጋጁ ከፕሮሞተሩ ጋር የዉል ስምምነት በመፈራረም በህጉ መሰረት ተግባብተዉ የንግድ ትርኢትና ባዛሩን መፈጸም እንዲችሉ የጋራ የስምምነት መፈራረምና ውል መግባት አለባቸዉ፤

18/ በቴሌቶን፣ በኤግዚቢሽን፣ በባህል ትውውቅ፣ በልማት ምረቃ፣ በቱሪዝም እና በመሳሰሉት ተያያዥ ጉዳዮች በሚል ስም የንግድ ትርኢትና ባዛር እንዲሁም የምርት ሽያጭ ማካሄድ አይቻልም፤

19/ አዘጋጁ በዚህ አፈፃፀም መመሪያ ውስጥ የተዘረዘሩትንና የሚጠይቃቸውን ጉዳዮች በማጤን የንግድ ትርኢቱን በተፈቀደለት አላማ መሠረት ተግባራዊ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡ በዚህ መሰረት ግዴታዎቹን መፈጸም ካልቻለ ፈቃድ ሰጪዉ በማንኛውም ጊዜ ህጋዊ ርምጃ እንዲወሰድበት በህግ የመጠየቅ መብት አለዉ፤

20/ አንድ አዘጋጅ በአንድ ከተማ/ወረዳ ከአንድ ጊዜ በላይ የንግድ ትርኢትና ባዛር ማካሄድ አይችልም፡፡ ይህም ለሌሎች አዘጋጆች እድል ለመስጠት ያስችላል፡ሆኖም ግን በዚያው ከተማ/ወረዳ ሌላ አዘጋጅ ካልጠየቀ አንድ ጊዜ አዘጋጅቶ የነበረው አካል በልዩ ሁኔታ ለሁለተኛ ጊዜ ሊያዘጋጅ ይችላል፤

21/ በየደረጃው የሚገኙ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት፣ የአነስተኛና መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች፣

ህብረት ስራ ማህበራትና ዩኒየኖች የንግድ ትርኢትና ባዛር ፈቃድ ሲጠይቁ ልዩ ፈቃድ ከንግድና ገበያ ልማት ቢሮ መውሰድ ይጠበቅባቸዋል፤

22/ የኤግዚቢሽን ፈቃድ የጠየቀ አዘጋጅ ፈቃዱን ለማውጣት የአገልግሎት ክፍያ ብር 150/አንድ መቶ ሀምሳ ብር/ ለፈቃድ ሰጭው ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ መክፈል ይኖርበታል፤

23/ የኤግዚቢሽን ፈቃድ የቆይታ ጊዜ በአንድ ከተማ/ወረዳ/ ላይ ከ 5 ተከታታይ ቀናት መብለጥ የለበትም፡፡ ሆኖም በአዘጋጅ አካል ጥያቄው ሲቀርብና መራዘሙ አስፈሊጊ ሆኖ ሲገኝ ፈቃዱን የሰጠዉ አካል ካመነበት እንዲስፈሊጊነቱ እስከ 2 ቀናት ሉራዘም ይችላል፡፡ የተፈቀደውን ተጨማሪ 2 ቀናት አልፎ በራሱ ጊዜ ኤግዚቢሽኑን ያስቀጠለ አዘጋጅ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፤

24/ ማንኛውም የኤግዚቢሽን ፈቃድ የተሰጠው አካል በኤግዚቢሽን ቆይታው ጊዜው የምርት ሽያጭ ማካሄድ የተከለከለ ነው፤

25/ የባዛር ፈቃድ የተሰጠው አዘጋጅ ፈቃዱን ማከራየትና ወደሌላ አካል ማስተላለፍ የተከለከነ ነው፡፡ ይሄን በሚያደረርግ አዘጋጅ ቢሮው ተከታትሎ አስፈላጊውን ርምጅ ይወስዳል፤

26/ የንግድ ትርኢትና ባዛር ፈቃድ በተሰጠበት ከተማ በዚያው ተመሳሳይ ቀናት የኤግዚቢሽን ፈቃድ መስጠት አይቻልም፡፡ በተዘዋዋሪም የኤግዚቢሽን ፈቃድ በተሰጠበት ከተማ በዚያው ተመሳሳይ ቀናት የንግድ ትርኢትና ባዛር ፈቃድ መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

8. በቢሮው ስለሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች

አዘጋጁ በመመሪያው ከተፈቀደው ውጭ የንግድ ትርኢትና ባዛር እያካሄደ መሆኑ ሲረጋገጥ ቢሮው ድርጊቱን በጥሞና በመመርመር የሚከተለትን እርምጃዎች ይወስዳል፦

1/ የንግድ ትርኢቱ እንዳይካሄድ ወይም በመካሄድ ላይ ያለው የንግድ ትርኢትም ቢሆን እንዲቋረጥ የማድረግ፤

2/ ከመመሪያዉ ዉጪ ሲንቀሳቀስ የተገኘ አዘጋጅ ከ1 ዓመት እስከ 2 ዓመት_የንግድ ትርኢትና ባዛር እንዳያካሂድ ይታገዳል፤

3/ እንደአስፈሊጊነቱ እየታየ ቢሮዉ የንግድ ትርኢትና ባዛር አዘጋጁን አካል ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት ክስ እንዲመሰርትበት ያደርጋል፤

4/ የንግድ ትርኢትና ባዛር ተሳታፊ ድርጅቶች በመመሪያዉ ከተቀመጠዉ አሰራር ዉጪ ሲንቀሳቀሱ ከተገኙ ሸቀጣቸው በኤግዚቪት ተይዞ ግለሰቦቹ ከባዛሩ እንዲወጡ በማድረግ አስፈላጊው ርምጃ እንዲወሰድባቸው ይደረጋል፤

5/ ያለ ፈቃድ ባዛር ያዘጋጅ አካል ቢገኝ ቢሮው በህግ የሚጠይቀውና እስከ ሁለት

ዓመት ጊዜ ውስጥ በክልሉ በሚካሄደው ባዛር እንዳይሳተፍ እገዳ የማድረግ፤

6/ ከተሰጠው ቀን ውጭ በማራዘም ወይም አስቀድሞ በመጀመር የሚሳተፍ ማንኛውም አዘጋጅ አካል ለመጀመሪያ ጊዜ የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ በቢሮው በኩል የሚሰጠው ሲሆን በድጋሚ ይሄንን ስህተት ከፈጸመ ለአንድ ዓመት በክልሉ በሚካሄደው ባዛር እንዳይሳተፍ እገዳ የማድረግ፤

7/ ማንኛውም በባዛር ላይ ተሳታፊ የሆነ ፕሮሞተር በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን ህጎች በመሻር ሲፈጽም ከተገኘ እንደየጥፋቱ ክብደት እየታየ ላልተወሰነ ጊዜ በክልሉ በሚካሄደው ባዛር እንዳይሳተፍ እገዳ የማድረግ፣ በህግ የመጠየቅ እና የንግድ ስራ ፈቃዱን እንዲሰረዝ ይደረጋል።

ክፍል ሶስት

ስለፈቀድ አሰጣጥና የተለያዩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

9. ፈቃድ ለመጠየቅ የሚቀርብ ማመልከቻ

ተጓዥ የሆነ ወይም ተጓዥ ያልሆነ የንግድ ትርኢትና ባዛር ለማዘጋጀት የሚቀርብ ማመልከቻ፦

1/ አድራሻው ለክልሉ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ መሆን አለበት፤

2/ የንግድ ትርኢትና ባዛሩ አላማ በግልጽ የሚያሳይ መሆን አለበት፤

3/ የአዘጋጁን ስምና ሙሉ አድራሻ መግለጽ አለበት፤

4/ የንግድ ትርኢቱ የሚካሄድበትን ቦታና የቆይታ ጊዜ መግለጽ ይኖርበታል፤

5/ የንግድ ትርኢትና ባዛሩ ማስፈጸሚያ እቅድ የሚከናወኑ ዝርዝር ተግባራትን፣ ሊሰበሰብ የሚችለዉን ገቢ እና አጠቃላይ ወጪ ሊያሳይ የሚችልና የፕሮሞተሩንና የአዘጋጁን የትርፍ ክፍፍል በግልጽ የሚያሳይ መሆን አለበት፤

6/ ማመልከቻዉ በፈቃድ ጠያቂው ወይም በሕጋዊ ወኪል ተፈርሞ መቅረብ ይኖርበል።

10. ልዩ ፈቃድ ለመጠየቅ የሚቀርብ ማመልከቻ

ልዩ የንግድ ትርኢትና ባዛር ፈቃድ ለማዘጋጀት የሚቀርብ ማመልከቻ፤

1/ አድራሻው ለክልሉ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ መሆን አለበት፤

2/ የንግድ ትርኢትና ባዛሩ አላማ በግልጽ የሚያሳይ መሆን አለበት፤

3/ የአዘጋጁን ስምና ሙሉ አድራሻ መግለጽ አለበት፤

4/ የንግድ ትርኢቱ የሚካሄድበትን ቦታና የቆይታ ጊዜ መግለጽ ይኖርበታል፤

5/ ማመልከቻዉ በፈቃድ ጠያቂው ወይም በሕጋዊ ወኪል ተፈርሞ መቅረብ ይኖርበት፤

6/ የድጋፍ ደብዳቤ ከከተማው ከንቲባ ወይም ከወረዳ አስተዳዳሪው መቅረብ ይኖርበታል፡፡

11.የንግድ ኤግዚቢሽን ለመጠየቅ የሚቀርብ ማመልከቻ

1/ አድራሻው ለክልሉ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ መሆን አለበት፤

2/ የንግድ ኤግዚቢሽኑን አላማ በግልጽ የሚያሳይ መሆን አለበት፤

3/ የአዘጋጁን ስምና ሙሉ አድራሻ መግለጽ አለበት፤

4/ የንግድ ኤግዚቢሽኑ የሚካሄድበትን ቦታና የቆይታ ጊዜ መግለጽ ይኖርበታል፤

5/ ማመልከቻዉ በፈቃድ ጠያቂው ወይም በሕጋዊ ወኪል ተፈርሞ መቅረብ ይኖርበታል፤

6/ የድጋፍ ደብዳቤ ከከተማው ከንቲባ ወይም ከወረዳ አስተዳዳሪው መቅረብ ይኖርበታል፤

7/ የፕሮሞተር ውል ስምምነት መቅረብ አለበት፡፡

12.የንግድ ትርኢትና ባዛር ስለማቋረጥ

የተከፈተው የንግድ ትርኢትና ባዛር ሊቋረጥ የሚችለው አንድም ከአቅም በላይ የሆኑ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ችግሮች ሲያጋጥሙ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ባዛሩ አሰራሩን ያልተከተለ መሆኑን ቢሮው ካረጋገጠ በቢሮ ኃላፊ ውሣኔ ይሆናል፡፡

13.የፈቃድ ሰጪው መ/ቤት እና የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

1/ የፈቃድ ሰጪው መ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት፦

ሀ) በከተማው ውስጥ ለሚካሄድ የንግድ ትርዒትና ባዛር፣ ልዩ የባዛር ፈቃድ እና ኤግዚቢሽን ፈቃድ ይሰጣል፤

ለ) ፈቃዱ አሰጣጡን በተመለከተ የክልሉ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ ዳይሬክቶሬት ሰነዱን መርምሮ መሟላት ያለበትን በማረጋገጥ ከአዘጋጁ ጋር ውል ይወስዳል፣ የአገልግሎት ክፍያ ያስከፍላል፣ ለቢሮ ኃላፊው ፈቃዱ እንዲሰጥ ያቀርባል፤

ሐ) የንግድ ቢሮ ኃላፊ ወይም ም/ቢሮ ኃላፊ ወይም ተወካይ ፈቃዱን ፈርሞ ይሰጣል፤

መ) የንግድ ትርዒትና ባዛር በሚካሄድበት ወቅት ክትትል ማድረግ፤

ሠ) በዚህ የአፈፃፀም መመሪያ ከተመለከቱት ውጭ የተካሄደ የንግድ ትርዒትና ባዛር መሆኑን ሲያረጋግጥ እና ባለድርሻ አካላት በደብዳቤ ለቢሮው ሲያሳውቁ በዚህ መመሪያ አንቀፅ 8 የተመለከቱትን እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

2/ የወረዳ/ከተማ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት፦

ሀ) ባዛር ለሚያካሂዱ አዘጋጆች የድጋፍ ደብዳቤ ይሰጣል፤

ለ) ባዛሩ በማኪሄድባቸው ቀናት የጸጥታና ሌሎች ተያያዥ ችግሮች እንዳይፈጠሩ ስምሪት ይሰጣል፣ ይከታተላል፤

ሐ) ባዛሩ የሚካሄድባቸውን ቦታዎች ይፈቅዳል፣ ለዝግጅቱ ምቹ መሆኑን ድጋፍ ያደርጋል::

3/ የገቢዎች ተቋም ተግባርና ኃላፊነት፦

ሀ) ግብይት በደረሰኝ መከናወኑን ይቆጣጠራል፣ ከተሳታፊ ነጋዴዎች መካከል ደረጃ ሀ እና ደረጃ ለ የሆኑትን ይለያል፤

ለ) በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ተገቢውን እርምጃ መውሰድ፤

4/ በየደረጃው የሚገኙ የጸጥታና ደንብ ማስከበር አገልግሎት ተቋም ተግባርና ኃላፊነት፦

ሀ) ከባዛሩ ዋዜማ ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ሁከትና ብጥብጥ እንዳይፈጠር ጥበቃ ያደርጋል፤

ለ) ወደ ባዛር የሚገቡ ተሳታፊዎችን ፍተሻ ያደርጋል፤

ሐ) ማንኛውም የንግድ ትርዒትና ባዛር ከፈቃድ ሰጪው አካል ፈቃድ ሳይሰጠው ሲዘጋጅ/ሲካሄድ ካገኘ የንግድ ትርዒትና ባዛሩን በማስቆም ህጋዊ እርምጃ እንዲወሰድበት ማድረግ፤

መ) በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ተገቢውን እርምጃ መውሰድ፤

5/ የጤና ተቋም ተግባርና ኃላፊነት፦

ሀ) በዝግጅቱ ላይ የሚቀርቡ ምርቶች በህብረተሰቡ ጤና ላይ ጉዳት የማያስከትሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

ለ) በሕግ በተሰጠው ስልጣን መሠረት ተገቢውን እርምጃ መውሰድ፤

6/ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ተቋም ተግባርና ኃላፊነት፦

በንግድ ትርኢትና ባዛር፣ ኤግዚቢሽን ላይ የሚቀርቡ ምርቶች የተሳታፊዎች ምርቶች መሆናቸወን ማረጋገጥ፡፡

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

14.የመተባበር ግዴታ

1/ ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ አፈጻጸም የመተባበር ግዴታ አለበት፤

2/ ማንኛውም ሰው የዚህን መመሪያ ድንጋጌ ተላልፎ ቢገኝ እንደየአግባቡ አስተዳደራዊ፣ ፍትሐብሄራዊና የወንጀል ተጠያቂነት ይኖርበታል፡፡

15.ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች

1/ የንግድ ትርኢትና ባዛር ማስፈጸሚያ መመሪያ ቁጥር 03/2005 በዚህ መመሪያ ተሽሯል፤

2/ ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረኑ ሌሎች መመሪያዎች ተፈጻሚነት የላቸውም፡፡

16.መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

1/ ይህ መመሪያ ከህዳር 25/2011 ዓ/ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተገለጸው ቢኖርም ይህ መመሪያ እንደገና አዲስ ቁጥር ከተሰጠበት ቀን በኋላ የሚነሳ መብት ወይም ግዴታ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው መመሪያው በፍትህ ቢሮ ተመዝግቦ በአስተዳደር ተቋሙ ድረ-ገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

አገኘሁ ተሻገር

የአብክመ ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ኃላፊ